## በሴት ልጅ ግርዛት በተመለከተ በሞላው አስተዳደር ግዛቶችና ተሪቶርዮች የሚቀርብ ድጋፍ፣ ምክርና መረጃ አሉ። በአቅራቢያዎ ያለን አገልግሎት አቅራቢ ለማግኘት ከዚህ በታች ያለን ይመልከቱ :



**Queensland**
Odette Tewfik
Multicultural Women's Health
*(የመድብለ ባህላዊ የሴቶች የጤና ጥበቃ ፕሮጀክት አስተባባሪ)*
Project Coordinator
True
**ስልክ:** 07 3250 0250
odette.tewfik@true.org.au

**Northern Territory**
Kirsten Thompson
Nurse *(ነርስ)*
Family Planning & Welfare
**ስልክ:** 08 8948 0144
kirsten.thompson@fpwnt.com.au

**New South Wales**
Linda George
Senior Health
Education Officer
*(የበላይ ጤና ጥበቃ ትምህርት ሃላፊ)*
NSW Education
Program on FGM
**ስልክ:** 02 9840 3910
linda.george@health.nsw.gov.au

**Western Australia**
Carol Kaplanian
FGM & FDV Research
Project Officer
*(ፕሮጀክት ሀላፊ)*
Women and Newborn
Health Service
**ስልክ:** 08 9340 1557
carol.kaplania@health.wa.gov.au

**ACT**
Esther Lam
CALD Liaison Nurse
*(CALD አገናኝ ነርስ)*
ACT Health
**ስልክ:** 02 6205 1078
esther.lam@act.gov.au

**South Australia**
Kim Voss
Social Worker
*(ማሕበራዊ ሰራተኛ)*
Women's Health Central
**ስልክ:** 08 8444 0700
kim.voss@health.sa.gov.au

**Tasmania**
Xavier Lane-Mullins
Community
Development Worker
*(የማህበረሰብ እድገት ሰራተኛ)*
**ስልክ:** 03 6235 6001
xlanemullins@redcross.org.au
Michou Kadima
Community
Development Worker
*(የማህበረሰብ እድገት ሰራተኛ)*
**ስልክ:** 03 6326 0400
mkadima@redcross.org.au

**Victoria**
Medina Idriess
FARREP Worker
*(FARREP ሰራተኛ)*
Royal Women's Hospital
**ስልክ:** 03 8345 3058
Farrep.program@thewomens.org.au

የ NETFA ፕሮጀክት የሚካሄደው በመድብለ ባህላዊ ማእከል ለሴቶች ጤና ጥበቃ ሲሆን የገንዘብ እርዳታ የሚያገኘው በኮመንዌልዝ መንግሥት ይሆናል። ለበለጠ መረጃ በድረገጽ www.NETFA.com.au ላይ ማየት ወይም በእኛ Twitter @EndFGM_NETFA መከታተል።

ተሻሽሎ የወጣበት ቀን: ሐምሌ/July 2016

**Amharic**

NETFA

# የሴት ልጅ ግርዛት

የሴት ልጅ ግርዛት ነባር ባህላዊ ልምድ ነው። ይህ ሆነ ተብሎ ውጫዊ የሴት ብልት መቁረጥ ወይም መለወጥ ነው። የሴት ልጅ ግርዛት አንዳንድ ጊዜ የሴት ልጅ ብልት መቁረጥ ወይም የሴት ብልት ጉዳት/መተልተል በሚል ይጠራል።

የሴት ልጅ ግርዛት በሴቶችና በልጃገረዶች ላይ ምንም የጤና ጥቅም የለውም እንዲሁም በወሲባዊ ግንኙነትና በስነተዋልዶ ጤና ላይ ተጽእኖ ሊያሳድር ይችላል።

ሰውነታችንን ለመቆጣጠርና ለመከላከል፣ ሁላችንም በክብር መስተናገደ አለብን። እንደ ሰብአዊ ፍጡር ይህ የእያንዳንዱ መብት ነው።

## ጤናን በተመለከቱ ጉዳዮች

የሴት ልጅ ግርዛት በጤና ላይ የአጭርና የረጅም ጊዜ ከሚከሰት ችግሮች ከዚህ በታች ያለን ያካትታል :

- *ከባድ ህመም*
- *ትኩሳት*
- *ጠባሳ መፍጠር*
- *የነርብ መቆጣት/ህመም (በነርብ ህዋሳት ላይ እብጠት ወይም ቁስል)*
- *የፋኛና የሽንት ቁስለት*
- *በሚሸኑበት ጊዜ ህመም*
- *በወር አበባ ጊዜ ወይም በወሲባዊ ግንኙነት ጊዜ ህመም*
- *በሽንት መተላለፊያ ቧንቧ ላይ ቁስለት*
- *ህጻን በሚወልዱበት ጊዜ ችግሮች ማለት እንደ የእምስ ቀዳዳ ጥበትና ጠባሳ ስላለ የማህጸን መቀደድ ይፈጠራል።*
- *ሞት*

## ሰብአዊ መብቶች

የሴት ልጅ ግርዛት እንደ በአለም አቀፍ የሴቶችንና ልጃገረዶችን ሰብአዊ መብታቸውን ህግ መጣስ ይቆጠራል።

# የሴት ልጅ ግርዛት የሚካሄደው የት ነው?




በዓለም ዙሪያ 200 ሚሊዮን የሚሆኑ ሴቶችና ልጃገረዶች የሴት ግርዛት እንደተደረገ ነው። ይህ ልምድ በአፍሪካ፤ ማእከላዊ ምሥራቅና በሳውዝ ኣሜሪካ ባሉት ማህበረሰባትና አንዳንድ የጎሳ ቡድኖች ሊገኝ ይችላል ይህም የሚከተሉትን ያካተተ ነው :

| | | | |
|---|---|---|---|
| በኒን | ኢትዮጵያ | ማሊ | ስታት ኦፍ ፓለስቲን እና እስራኤል |
| ቡርኪና ፋሶ | ጋምቢያ | ሞሪታኒያ | ሱዳን |
| ካመሩን | ጋና | ናይጀር | ታንዛኒያ |
| ሰንትራል አፍሪኻን ሪፑብሊክ | ጊኒያ | ናይጀሪያ | ቶጎ |
| ቻድ | ጉኒያ - ቢሳው | ኦማን | ኡጋንዳ |
| ኮሎምቢያ | ህንድ | ፓኪስታን | ዩናይትድ አረብ ኢሚራትስ |
| ኮተ ዲ' ኢቮረ | ኢንዶነሺያ | ፐሩ | የመን |
| ኮንጎ ዲሞክራቲክ ሪፑብሊክ | ኢራን | ሰነጋል | ዛምቢያ |
| ጅቡቲ | ኢራክ | ሰራ ሊዮን | |
| እኳዶር | ኬኒያ | ሲንጋቦር | |
| ግብጽ | ላይቨሪያ | ሶማሊያ | |
| ኤርትራ | ማላያዥያ | ስሪ ላንካ | |

ለሴት ልጅ ግርዛት የተጀመረው እንደማይታወቅና በሃይማኖት ጠቀሜታ አለው። የሴት ልጅ ግርዛት ዓይነቶች በማህበረሰቦችና በጎሳ/ብሄር ቡድኖች መካከል የተለያየ ነው። በዓለም ዙሪያ ያሉት አገሮች የዚህን ዓይነት ድርጊት እንዳገዱትና በህገወጥነት እንዳስቀመጡት ነው። ስላለን ባህላዊ ልምዶች መነጋገርና መወያየት አስፈላጊ ነው። ባህላችንን እንወዳለን፤ ነገር ግን ለሌላው ጉዳት ሊያመጣ የሚችለውን ልምድ ማስወገድ ይኖርብናል።

## 4 የሴት ልጅ ግርዛት ዓይነቶች

**ዓይነት/Type 1 ወይም** Sunna ኪንጥርን በከፊል ወይም ሁሉንም ማስወገድ (የሴት ብልትን ትንሽ፣ ስሜታዊ የሆነን ክፍል) ወይም የቂንጥርን ሽፋን (በቂንጥሩ ዙሪያ ያለን ቆዳ)።

**ዓይነት/Type 2 ወይም** Sounna ኪንጥርንና ትንሹን ከንፈር የመሰለን ብልት በከፊል ወይም ሁሉንም ማስወገድ (በሴት ብልት ውስጥ ያለን ከንፈር መሳይ ሽፋን ቆዳ) ይህም ከትልቁ ከንፈር የመሰለን ብልት (በሴት ብልት የሚሸፍን ትልቅ የታጠፈ ቆዳ) ጋር ወይም ሳይጨምር ማስወገድ።

**ዓይነት/Type 3 ወይም** መዝጋት/Infibulation (Pharaonic) በእምስ ዙሪያ ያለን ትንሹንና ትልቁን ከንፈር የመሰለ ብልት በከፊል ወይም ሁሉንም ማስወገድና በእምስ ዙሪያ ትንሽ ቀዳዳ ለሽንትና ለወር አበባ መውጫ ብቻ በመተው መለጠፍና ማሽግ። ዓይነት/Type 3 አሰራር ቂንጢርን በማውጣት ወይም ባለማውጣት ይካሄዳል።

**ዓይነት/Type 4 ወይም** የሚያካትተው ሁሉንም የሴት ብልት ዙሪያ ይህም ለህክምና ላልሆነ ምክንያት የመንደልን፣ መውጋት፣ ንቅሳት፣ መጫር፣ ብልትን ማራዘምና ማጨማደድን ያካትታል።

ዓይነት/Type 3 ወይም ብልትን መዝጋት/Infibulation የሚካሄደው በዓለም ዙሪያ ካሉት ሴቶች ውስጥ በግምት 10% ለሴት ልጅ ግርዛት በማካሄድ ነው። የማዘጋት ግርዛት ያካሄዱ ሴቶች እንዲከፈትላቸው ለሀኪማቸው ወይም ለሆስፒታል ማነጋገር ይችላሉ። እንዲሁም 1, 2 ወም 4 ከባድ ላይሆን ቢችልም ነገር ግን በግለሰቡ ጤናና ደህንነት ችግር ሊፈጥር ይችላል።

## በአውስትራሊያ ውስጥ የሴት ልጅ ግርዛት ህገ-ወጥነት ነው።

*ለሚከተለው ማካሄድ ህገ-ወጥ ነው :*

- *ማንኛውንም የሴት ብልት አካልን ማስወገድ ወይም መቁረጥ*
- *በሴት ብልት አካባቢ መሰፋት ወይም እንደገና መሰፋት*
- *የሴት እምስን ክፍተት ማጥበብ*
- *ቂንጢርን መቁረጥ ወይም መውጋት*
- *በሴት ብልት አካባቢ ጉዳት ወይም ችግር መፍጠር*

*አንድ ሰው ለሚከተለው ማካሄድ ህጉ አይፈቅድለትም :*

- *ማየሴት ወይም የልጃገረድ ህጻን ብልት መቁረጥ*
- *አንድን ሰው ለማስቆረጥ ከአውስትራሊያ ውጭ መውሰድ*
- *አንድን ሰው ለማስቆረጥ ከአውስትራሊያ ውጭ ለማስወጣት የሚረዳ*

*አንድ ሰው የሚከተሉትን ካደረገ ህግ እየጣሰ ነው፥ :*

- *ድርጊቱን ካካሄዱ*
- *ድርጊቱን ለማካሄድ ከረዱ*
- *ድርጊቱን የማካሄድ የሆነ ሰው ላገኙ*

**የሴት ልጅ ግርዛት ማካሄድ እስከ 21 ዓመታት የእስራት ቅጣት ይኖረዋል።**